# ዳሎል አይል አክሲዮን ማህበር የመመስረቻ ጽሁፍ

## ምሥረታ

ስማችን፣ ዜግነታችንና አድራሻችን በዚህ የመመሥረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው መስራች አባላት በሥሩ የተለያየ የንግድ ሥራ የሚያከናውን አክሲዮን ማህበር ለማቋቋም በ1952 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣ በዚህ የመመሥረቻ ጽሁፍና ከዚህ ጋር በአባሪነት በተያያዘው የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት እንደሚከተለው ተስማምነተናል፡፡

## አንቀጽ አንድ

## የባለአክስዮኖች ስም፣ዜግነትና አድራሻ

የማህበሩ መስራች አባላት ስማችን ዜግነታችንና አድራሻችን ከዚህ በታች በሠንጠረዥ የተገለፀው ነው፡፡

| ተ.ቁ | ስም | ዜግነት | አድራሻ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከተማ | ክ/ከተማ | ቀበሌ | የቤት.ቁ |
| 1 | ፕሮፌሰር ባደግ በቀለ | ዜግነት አሜሪካዊ በትውልድ ኢትዮጵያዊ | አ.አ | ልደታ | 02/03 | 211 |
| 2 | አቶ ደረጀ በላይ ይስማው | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | ቂርቆስ | 05/06/07 | 384 |
| 3 | አቶ ፍስሀ አስረስ ገብረመድህን | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | ቦሌ | 15 | አዲስ |
| 4 | አቶ ነብያት ገዛኸኝ ደስታ | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | ቦሌ | 17/19/20 | አዲስ |
| 5 | አቶ ደረጀ ዋለልኝ መራ | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | ቂርቆስ | 03 | 536 |
| 6 | አቶ ኢዲዲያ አስፋ ዙርጋ | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | ቂርቆስ | 15/16 | 102/44 |
| 7 | አቶ ገብረአምላክ ገብረጊዮርጊስ ተክለ | ኢትዮጵያዊ | አ.አ | ቦሌ | 14/15 | 140/32 |

## አንቀጽ ሁለት

## የማህበሩ መጠሪያ

የማህበሩ መጠሪያ ስም ዳሉል አይል አክሲዮን ማህበር ነው።

## አንቀጽ ሦስት

## የማህበሩ አድራሻ

3.1 የማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ አ.አ ቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 04 የቤት ቁጥር አዲስ (የአምባሰል የንግድ ስራዎች ህንፃ 2ኛ ፎቅ) ነው።

3.2 ማህበሩ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በኢትዮጵያ ውስጥና በውጪ ሀገር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ማቋቋም ይችላል።

## አንቀጽ አራት

## የማህበሩ አላማዎች

ማህበሩ የተቋቋመበት ዓላማዎች፤

4.1 ነዳጅ እና የነዳጅ ምርቶችን ማከፋፈል እና ማሰራጨት

4.2 የነዳጅ ዘይቶችን እና ቅባቶችን ወደ ሃገር ውስጥ ማስገባት ፤ ማከፋፈል እና ማሰራጨት

4.3 የነዳጅ ማደያ ጣቢያ አገልግሎቶችን ማካሄድ

4.4 ነዳጅ እና የነዳጅ ምርቶችን ማጓጓዝ

4.5 የነዳጅ ፍለጋ፤ማውጣት እና ማጣራት ስራዎችን ማካሄድ

4.6 ከአክሲዮን ማህበሩ የሥራ ዘርፍ ዓላማ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ስራዎችን ማከናወን።

## አንቀጽ አምስት

## የማህበሩ ካፒታል

5.1 የማህበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር 1400,000/አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ / ነው።

5.2 የተከፈለው የማህበሩ ካፒታል ብር 350,000 (ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ ሲሆን ይኸው ገንዘብ በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል።

5.3 የማህበሩ ያልተከፈለ ካፒታል ብር 1050,000/አንድ ሚሊየን ሃምሳ ሺህ/ ሲሆን ይህ ያልተከፈለው የማህበሩ ካፒታል ማህበሩ ከተቋቋመበት ቀን ጀምሮ በ3 ወራት ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ መከፈል አለበት።

5.4 የማህበሩ የተፈረመ ካፒታል እያንዳንዳቸው ብር 1,000.00 /አንድ ሺህ/ ዋጋ ባላቸው 1400 አክስዮኖች ተከፋፍሏል።የማህበሩ አክስዮኖች ከ1-1400 ተራ ቁጥር ተሰጥቶዋቸዋል።

5.5 ከፍተኛው የአክስዮን መጠን ከጠቅላላው መጠን ሃያ በመቶ (20%) ይሆናል።

5.6 ህጋዊ ዝምድና ባላቸው አባላት ሊያዝ የሚችለው የአክሲዮን መጠን በ5.5 ከተገለጸው ሀያ በመቶ ሊበልጥ አይችልም።

## አንቀጽ ስድስት

## የአክሲዮኖች መዋጮና የአክሲዮን ድልድል

በመስራች አባላት የተያዘው የአክስዮን መጠን የሚከተለው ነው።

| ተ.ቁ | ስም | የአክስዮን ድርሻ | የአንድ አክስዮን ዋጋ | የተፈረመ ካፒታል በጥሬ ገንዘብ በብር | የተከፈለ የአክሲዮን ዋጋ | ያልተከፈለ የአክሲዮን ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ በብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፕሮፌሰር ባደግ በቀለ | 200 | 1,000 | 200,000 | 50,000 | 150,000 | 200,000 |
| 2 | አቶ ደረጀ በላይ ይስማው | 200 | 1,000 | 200,000 | 50,000 | 150,000 | 200,000 |
| 3 | አቶ ፍስሀ አስረስ ገብረመድህን | 200 | 1,000 | 200,000 | 50,000 | 150,000 | 200,000 |
| 4 | አቶ ነብያት ግዛቸኝ ደስታ | 200 | 1,000 | 200,000 | 50,000 | 150,000 | 200,000 |
| 5 | አቶ ደረጀ ዋለልኝ መራ | 200 | 1,000 | 200,000 | 50,000 | 150,000 | 200,000 |
| 6 | አቶ ኢዲዲያ አሰፋ ዙርጋ | 200 | 1,000 | 200,000 | 50,000 | 150,000 | 200,000 |
| 7 | አቶ ገብረአምላክ ገብረጊዮርጊስ ተክለ | 200 | 1,000 | 200,000 | 50,000 | 150,000 | 200,000 |
| | ጠቅላላ ድምር | 1400 | ------- | 1,400,000 | 350,000 | 1,050,000 | 1,400,000 |

## አንቀጽ ሰባት

## የባለአክስዮኖች ኃላፊነት

7.1መስራቾች ለማህበሩና ለ3ኛ ወገኖች በአንድነት ሳይከፋፈል ለሚደርሱ ጉዳቶች ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

7.2 የማህበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ እንዲገባና ለማቋቋሚያውም አስፈላጊለው ገንዘብ ገቢ ስለመሆኑ ያረጋግጣሉ፡፡

7.3 ባለአክስዮኖች ኃላፊነታቸውን በማህበሩ ውስጥ ባላቸው የአክስዮን ድርሻ ነው፡፡

## አንቀጽ ስምንት

## የትርፍና ኪሣራ ክፍፍል

አባላቱ በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር ከጠቅላላው ዓመታዊ ትርፍ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ እና ሌሎች ጠቅላላ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ ቀሪው በአባላቱ መካከል እንደ አክስዮን ይዞታቸው ይከፋፈላል፡፡ ኪሳራም ካለ በተመሣሣይ ሁኔታ በአባላቱ መካከል ይከፋፈላል፡፡ ሆኖም በማንኛውም ሁኔታ አባላቱ በማህበሩ ውስጥ ካለው የአክስዮን ካፒታል በላይ ተጠያቂ ሊሆን አይችሉም፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ

## ስለ ማህበሩ አስተዳደር

9.1 የማህበሩ አስተዳደር ሥራ የሚሰጠው ለማህበርተኞች ብቻ ነው ፡፡

9.2 ማህበሩ የሚተዳደረው በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚመረጡ የማህበሩ አስተዳዳሪዎች ወይም የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት ነው ፡፡

9.3 ማህበሩ 7 አስተዳዳሪዎች አሉት፡፡ እንደአስፈላጊነቱ የማህበሩ አስተዳዳሪዎች ቁጥር 9 ሊደርስ ይችላል፡፡

9.4 ቦርዱ ኘሬዘደንት፣ ምክትል ኘሬዘዳንትና ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡

9.5 የአስተዳደር ምክር ቤት ወይም ቦርድ አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊሾም ይችላል፡፡

9.6 የአስተዳዳሪዎች ምክር ቤት / የዲሬክተሮች ቦርድ/ የሥራ ዘመን 3 ዓመት ብቻ ነው፡፡ የአዲስ ዲሬክተሮች ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ ከነባር አባላት 1/3 በአዲሱ አመራር ውስጥ እናዲያገለግሉ ይደረጋል

9.7 የአስተዳዳሪዎች ምክር ቤት አባላት የስራ ዘመናቸው ሲያበቃ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ለተጨማሪ የሥራ ዘመናት ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

9.8 በሥራው ዘመን ውስጥ አንድ ወይም ብዙ አስተዳዳሪዎች የጎደሉ እንደሆነ የቀሩት አስተዳደሪዎች ምትኮቻቸውን ይመርጣሉ፡፡ የተመረጡት ምትክ አስተዳዳሪዎች የሥራ ዘመን የሚያበቃው በፊት በነበሩበት አስተዳዳሪዎች የተሰጠውን የሥራ ጊዜ በሚያልቅበት ዘመን ነው፡፡

9.9 በንኡስ አንቀፅ 8 ስር የሚደረግ የምትክ አስተዳዳሪዎች ምርጫ በጠቅላላ ጉባኤ መጽደቅ አለበት፡፡ ጉባኤውም የነዚሁት አስተዳዳሪዎች ምርጫ ሊያጸድቅ ወይም ሌሎች አስተዳዳሪዎችን ሊመርጥ ይችላል፡፡

9.10 አስተዳዳሪዎች ወይም የቦርድ አባላት ሁሉ ሥራቸውን የተው እንደሆነ ሌሎች አስተዳዳሪዎችን ለመመረጥ ተቆጣጣሪዎቹ ጠቅላላውን ጉባኤ አስቸኳይ መጥራት አለባቸው፡፡

9.11 ንዑስ ቁጥር 10 መሠረት ጠቅላላ ጉባኤ እስኪሰበሰብ ድረስ ተቆጣጣሪዎች የአስተዳደሩን ሥራዎች መፈጸም ይችላሉ፡፡

9.12 ማንኛውም ተቃራኒ ቃል ቢኖረም በማናቸውም ጊዜ አስተዳዳሪዎቹ ወይም የቦርድ አባላት በጠቅላላ ጉባኤ ሊሻሩ ይችላሉ፡፡ መሻራቸው ትክክለኛ ምክንያት ያልያዘ እንደሆነ ግን አስተዳዳሪዎቹ የጉዳት ካሣ ለማግኘት መብት አላቸው፡፡

9.13 አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የዲሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ በኘሬዘዳንቱ ወይም በሥራ አስኪያጁ ሊጠራ ይችላል፡፡ የዲሬክተሮች ስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሌለ ዲሬክተር አይሰጥም፡፡ ዲሬክተሮች የማህበሩን ሥራ ያከሂዳሉ፡፡ ውሣኔያቸውም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 358 ድንጋጌ መሠረት ይመዘግባሉ፡፡

9.14 የአስተዳደር ምክር ቤት ወይም ቦርድ ውሣኔዎች ዋጋ ያላቸው እንዲሆኑ በሥራ ላይ ካሉት አስተዳዳሪዎች የሚበዙት ወይም አብዛኛዎቹ በጉባኤው እንዲገኙ አስፈላጊ ነው፡፡

9.15 ውሳኔዎቹም የሚደረጉት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ብልጫ ነው፡፡

9.16 የአስተዳደር ምክር ቤት ወይም የዲሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚከተሉት ሆነው በጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ ተመርጠዋል፤

ሀ. ፕሮፌሰር ባደግ በቀለ

ለ. አቶ ደረጀ በላይ ይስማው

ሐ. አቶ ፍስሀ አስረስ ገብረመድህን

መ. አቶ ነብያት ገዛኸኝ ደስታ

ሠ. አቶ ደረጀ ዋለልኝ መራ

ረ. አቶ ኢዲዲያ አሰፋ ዙርጋ

ሰ. አቶ ገብረአምላክ ገብረጊዮርጊስ ተክለ

## አንቀጽ አስር

## የዲሬክተሮች ቦርድ ስልጣን

በህግ በመመስረቻ ጽሁፍ እና በመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ የባለአክስዮኖች ጉባኤ ውሣኔ ለሌላ የማህበሩ አካል ተለይቶ ካልተሰጠ በቀር ለተለየ ሥራና ሁኔታ የሚያስፈልገው የማህበሩ ስልጣን ሁሉ የዲሬክተሮች ቦርድ ስልጣን ይሆናል። በንግድ ሕግ ቁጥር 362/364/ 446 እና 447 ሥር የተገለጹት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የዲሬክተሮች ቦርድ ከዚህ የሚከተለው ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

10.1 የማህበሩ እንቅስቃሴ መቆጣጠር፤

10.2 የማህበሩን ሥራ አስኪያጆች ለመሾም እንደአስፈላጊነቱ ለመቅጠር ለማሰናበትና ለማገድ እንዲሁም ደመወዝ አበል ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችንና የሥራ ሁኔታዎች መወሰን፤

10.3 በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መቋቋምን መወሰን

10.4 ማናቸውንም ተስማሚ ሆኖ ያገኘውንና የማህበሩን ገንዘብ ሥራ ላይ ስለማዋል ፤ ሂሣብ ለጠቅላላ የባለአክስዮኖች ስብሰባ ማቅረብ፤

10.5 የማህበሩን ጉዳይ ለማስፈጸም የሚችል የህግ ባለሙያ ህጋዊ መብት ያለውን ድርጅት ወይም ጉዳይ አስፈጻሚ የመወከል ።

10.6 የአስተዳደር ምክር ቤት ወይም ቦርድ አባላት ወደ ማህበሩ የሚገቡ አዲስ አባላትን ተቀብሎ መመዝገብ በቃለ ጉባኤ ይዞ በህጋዊ አካል እንዲጸድቅ ማድረግ፡፡

10.7 የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ እና መመስረቻ ጽሑፎችን በተሟላ አባላት ድምጽ ለማሻሻል ይችላል፡፡

10.8 የዲሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ስልጣኑን ለኘሬዝዳንት ለመስጠት ይችላል፡፡

10.9 የዲሬክተሮች ቦርድ ፀሐፊ ይሾማል፡፡ የዲሬክተሮች ቦርድ ውሣኔዎች በኘሬዚዳንቱና በፀሐፊው ተፈርመው በቃለ ጉባኤ መዝገብ ውስጥ ተመዝግበው ይቀመጣሉ፡፡

10.10 ዲሬክተሮች በንግድ ሕግ አንቀጽ 365 መሰረት በአንድነትና በነጠላ ለማህበሩ ለዕዳው ጠያቂዎች ኃላፊነት አለባቸው፡፡

10.11 ቦርዱ በክፉ ልቦና በተንኮል ወይም ከተሰጠው ስልጣን ውጪ ካልሰራ በቀር የተጣለበትን ኃላፊነት በመወጣት ወይም በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት ባገኘው ስልጣን ለሥራው ሥራ በህጋዊ መንገድ ሳከናወነው በግሉ ምንም ኃላፊነት አይኖርበትም፡፡

10.12 የማህበሩ ዳይሬክተሮች በማንኛውም ሁኔታ ከማህበሩ ገንዘብ ሊበደሩ ወይም ለግል ዕዳቸው በማህበሩ ሊጠቀሙ አይችሉም፡፡

10.13 የዲሬክተሮች የአገልግሎት ክፍያ በየዓመቱ በመደበኛ ጠቅላላ ስብሰባ ይወሰናል፡፡ ይህም ክፍያ ከጠቅላላ ውጪ ውስጥ ይጠቃለላል፡፡

10.14 በንግድ ሕግ 359 እና 360 ድንጋጌ መሰረት የዲሬክተሮች ምዝገባ ይኖራል፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ

## የመስራች አባላቶች ልዩ መብትና ጥቅም

9.1 የማህበሩ መስራቾች ከማህበርተኛነታቸው መብት በላይ መስራቾች ለ 3 ዓመት በሂሣብ ሚዛኑ መሠረት ከሚገኘው የተጣራ ትርፍ ውስጥ በጠቅላላው አስራ አራት (14%) ከመቶ ከተጣራው ትርፍ ይወስዳሉ፡፡

9.2 በንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ማህበሩ የንግድ ስራውን ከሚጀምርበት ( operational ከሚሆንበት) ጊዜ አንስቶ ነው፡፡

9.3 የማህበሩ መስራቾች ማህበሩ ስራ ከሚጀምርበት ጊዜ አንስቶ እስከ 4 ዓመት ድረስ አክሲዮኖችን በተግዜ ዋጋቸው (par value) መሠረት መግዛት ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ አስር

## ሥራ አመራር

10.1 ማህበሩ የአስተዳደር ሥራ የሚሰራ ከአባላት መካከል በባለአክሲዮኖች የሚመረጥ የሥልጣን ዘመኑ ያልተወሰነ አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ይኖረዋል፡

10.2 የማህበሩ አባል የሆኑት አቶ ኢዱዲያ አሰፋ ዙርጋ የማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው በባለአክሲዮኖች ተሾመዋል፡፡

10.3 የማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር በንግድ ሕግና በዚህ የመመሥረቻ ጽሁፍ በአንቀጽ 11 የተገለጸው ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አስራ አንድ

## የዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ፤

11.1 ማህበሩን በመወከል ይፈርማል

11.2 ለማህበሩን ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ተግባሮች ኃላፊ ነው፡፡

11.3 ቦርድ ውሳኔዎች ሥራ ላይ ያውላል

11.4 የማህበሩ የሚከፈል ገንዘብ መቀበል፣የማህበሩን ዕዳዎች መክፈል፣ ማናቸውም የሐዋላ ወረቀት፣ የተሰፋ ሰነድ፣ የባንክ ሰነድ ማዘጋጀትና በጀርባው ላይ መፈረም፣ ማደስና መክፈል እንዲሁም የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኞች፣ የቦንድ ሰርተፊኬቶችን ወይም ማናቸውንም ሰነዶች ማፅደቅና ከጀርባው መፈረም የመሳሰሉት ተግባራት ያከናውናል፡፡

11.5 የማህበሩን ወኪል ወይም ሰራተኛ ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣ ክፍያውን፣ ደሞዙን ጉርሻና ሌሎች ከመቀጠርና ከመሰናበት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ይወስናል፡፡

9.2 በንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ማህበሩ የንግድ ስራውን ከሚጀምርበት ( operational ከሚሆንበት) ጊዜ አንስቶ ነው፡፡

9.3 የማህበሩ መስራቾች ማህበሩ ስራ ከሚጀምርበት ጊዜ አንስቶ እስከ 4 ዓመት ድረስ አክሲዮኖችን በተፃፈ ዋጋቸው (par value) መሠረት መግዛት ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ አስር

## ሥራ አመራር

10.1 ማህበሩ የአስተዳደር ሥራ የሚሰራ ከአባላት መካከል በባለአክሲዮኖች የሚመረጥ የሥልጣን ዘመኑ ያልተወሰነ አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ይኖረዋል፡

10.2 የማህበሩ አባል የሆኑት አቶ ኢዲዲያ አሰፋ ዙርጋ የማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው በባለአክሲዮኖች ተሾመዋል፡፡

10.3 የማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር በንግድ ሕግና በዚህ የመመሥረቻ ጽሁፍ በአንቀጽ 11 የተገለጸው ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አስራ አንድ

## የዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ፤

11.1 ማህበሩን በመወከል ይፈርማል

11.2 ለማህበሩን ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ተግባሮች ኃላፊ ነው፡፡

11.3 ቦርድ ውሳኔዎች ሥራ ላይ ያውላል

11.4 የማህበሩ የሚከፈል ገንዘብ መቀበል፤የማህበሩን ዕዳዎች መክፈል፤ ማናቸውም የሐዋላ ወረቀት፤ የተሰፋ ሰነድ፤ የባንክ ሰነድ ማዘጋጀትና በጀርባው ላይ መፈረም፤ ማደስና መክፈል እንዲሁም የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኞች፤ የቦንድ ሰርተፊኬቶችን ወይም ማናቸውንም ሰነዶች ማዕደቅና ከጀርባው መፈረም የመሳሰሉት ተግባራት ያከናውናል፡፡

11.5 የማህበሩን ወኪል ወይም ሰራተኛ ይቀጥራል፤ ያሰናብታል፤ ክፍያውን፤ ደሞዙን ጉርሻና ሌሎች ከመቀጠርና ከመሰናበት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ይወስናል፡፡

11.6 በማህበሩ ስም የባንክ ሂሣቦች ይከፍታል ሂሳቡንም በዋና ስራ አስኪያጅና በሂሣብ ሹም በጋራ ፊርማ ይንቀሳቀሣል፡፡ ነገር ግን ማንኛውም ከ 500,000 ብር /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በላይ የሆነ ወጪ በቦርድ መወሰን አለበት፡፡ ሆኖም ይህ አንቀጽ ወደፊት እንደአስፈላጊነቱ በቦርድ ሊሻሻል ይችላል፡፡

11.7 ማህበሩ ንግድ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም የንግድ ልውውጥ በተመለከተ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ውል ይዋዋላሉ በማህበሩ ስም እስከ 500,000 ብር /አምስት መቶ ሺህ ብር/ የሚያወጣ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት የመግዛትና የማህበሩን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሣቀስ ንብረት መሸጥ እና መለወጥ፡፡ ነገር ግን ከ 500,000 ብር በላይ የሚያወጣ በማህበሩ ስም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት የመግዛት፣ የመሸጥ እና የመለወጥ በቦርድ ውሳኔ መደረግ አለበት፡፡

11.8 በማናቸውም ፍርድ ቤት ማህበሩ ከሳሽ፣ ተከሳሽ ወይም ጣልቃ ገብ በሚሆንበት ጉዳይ ሁሉ ማህበሩን በመወከል አስፈላጊውን ይፈጽማል፡፡

11.9 የማህበሩ ስራ ለማከናወን አስፈላጊ ሲሆን ከላይ ከተገለጹት ተግባራት መሀል ማናቸውንም በሌላ ለሦስተኛ ሰው እንዲፈጸም በማህበሩ ስም ውክልና መስጠት ይችላል፡፡

11.10 በማህበሩ ስም ተመዝግባ የሚገኙትን የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች በዋስትና በማስያዝ ከባንክ፣ ከግለሰቦች በአበዳሪ ድርጅቶች ይበደራል የብድር ውል ስምምነቶች ይፈጽማል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሁለት

## ተቆጣጣሪዎች /ኦዲተሮች/

ማህበሩ በአባላቱ የሚመረጡ ኦዲተሮች ይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ አስራሶስት

## ማህበሩ የሚቆይበት ጊዜ

ማህበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው ።

ይህ የመመሥረቻ ጽሁፍ በመስራች አባላት ተዘጋጅቶ፣ ተነቦና ፀድቆ ዛሬ ---------- ቀን

2001 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተፈርሟል።

| የመሥራች አባላት ስም | ፊርማ |
| --- | --- |
| 1. ፕሮፌሰር ባደግ በቀለ | ---------------------- |
| 2. አቶ ደረጀ በላይ ይስማው | ---------------------- |
| 3. አቶ ፍስሀ አስረስ ገብረመድህን | ---------------------- |
| 4. አቶ ነብያት ገዛኸኝ ደስታ | ---------------------- |
| 5. አቶ ደረጀ ዋለልኝ መሪ | ---------------------- |
| 6. አቶ ኢዲዲያ አሰፋ ዙርጋ | ---------------------- |
| 7. አቶ ገብረእምላክ ገብረጊዮርጊስ ተክለ | ---------------------- |

የፍትህ ሚኒስቴር ... Ministry of Justice Documents Authentication and Registration Office-B